የሁለተኛ ሳምንት የመፅሀፍ ግብዣችን ላይ እንገኛለን።

የረመዷን ወቅት ከመድረሱ ጋር ተያይዞ እልፍ አእላፍ ሙስሊሞች በፆም፣ በተውበት ወደ ጌታቸው የሚዋደቁበት መልካም ግዜ ነው። በዚህ ወቅት ብዙሀኖቻችን ወደ አላህ የምንመለስ ይሁን እንጂ የአሳሳባዊ አምልኳዊ ተግባራቶች (ዒባዳ) አፈፃፀም ላይ ያለን እውቀት አናሳ በመሆኑ እንሳሳታለን። እነዚህን ስህተቶች ለመግራት እጅግ አጠር ብለው በታላላቅ ሼኾች የተዘጋጁ መፅሀፎችን እንጋብዝዎ። እነርዚህ መፅሀፍት እጅጉን ያጠሩ እና ወሳኝ ትምህርትን የሚሰጡ ናቸው። መልካም ንባብ እንዲሆንልዎ እየተመኘን ስለ መፅሀፉ አጭር መግለጫ እነሆ!

መፅሀፍ አንድ!

የመፅሀፉ ስም - Al-Siyaam

አዘጋጅ ሼኽ ሙሀመድ ሷሊህ አል-ሙንጂድ!

የገፅ ብዛት 20

ሼኻው አላህ ከግፈኞች እስር እና በደል ነፃ ይበላቸውና ከደርዘን በላይ በሆነ ቋንቋ ፈተዋ የሚሰጥ ድህረ ገፅ መስራችና የብዙ መፅሀፍ ፀሀፊ ከዚያም በላይ ታላቅ መምህር እና ጠቢብ ናቸው። በዚህ 20 ገፅ በሚሞላው መፅሀፍ ስር ከፆም ጋር ተያያዥነት ያላቸው 70 ነጥቦችን ያነሳሉ። ለሚያነሷቸው ነጥቦች ቁርዐናዊ እና ሃዲሳዊ ነጥቦች ብርቱ ማስረጃዎቻቸው ናቸው። ከፊታችን የሚመጣውን ረመዳን አላህ እና መልእክተኛው ባዘዙት መልኩ ለመፆም ይህን መፅሀፍ መመልከት ትልቅ ጥቅም አለው።

መፅሀፍ ሁለት!

የመፅሀፉ ስም - How do I Repant
አዘጋጅ Educational Department of Dar Al-Watan
የገፅ ብዛት 16

በዚህ መፅሀፍ ስር ከተውበት ጋር የተያያዙ ወሳኝ ቁርዐናዊ እና ሀዲሳዊ መረጃዎች ተካተዋል። አዘጋጆቹ አጠር ባለ መልኩ ለምን ተውበት ማድረግ እንዳለብን እና ተውበታችንም አላህ ዘንድ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ በምን መልኩ መሆን እንዳለበት ይጠቁሙናል። ለአመታት በወንጀል የጠቆረች ነብሳችንን ለማንፃት ረመዳን እጅግ መልካም አጋጣሚ ሲሆን ምን ማድረግ እንዳለብን ደግሞ ይህ መፅሀፍ ይጠቁመናል።

አላህ ረመዳንን አጊንተው ከሚጠቀሙበት መልካም ባርያዎቹ ያድርገን!

አሚን